# ብርቱካን ትፈታ!

ወለላዬ ከስዊድን

“ብርቱካን ትፈታ!” ስንል እኛ ዛሬ
ምን ያህል እንደሆን ያለን ጥንካሬ
መፈተሽ አለብን እንዳንቀር በወሬ።

ህዝብ አዳራሽ ጠርተን አድርገን ስብሰባ
መለየት ከሆነ በደማቅ ጭብጨባ
ትርፍ የለንም ጭራሽ አንበቃም ለውጤት
ለመሥራት ካልቻልን ተባብረን በአንድነት።

አዎን ይፈቱልን የኅሊና እስረኞች
በሆነ ባልሆነው አይጠቁ ዜጎች
ብርቱካን ትፈታ ማንም አይታሰር
እኛም እንላበስ ሠላምና ፍቅር።




እነሱ ለክፋት ለተንኮል ሲስማሙ
ተባብሮ ለመሥራት እኛ አንሶናል አቅሙ
በአውሬ ተውጠን ወገባችን ድረስ
ለማን ሊረዳ ነው መፋጀቱ እርስ በርስ
ይልቅስ ያውሬውን የሰላ መንጋጋ
ባንድነት እንሰባብር ወድቀናል ካደጋ።
ጠላት እንደማጥቃት እኛው ስንነጫጭ
ምን ብሎ አብሮን ይቁም እንዴት ይመነን ነጭ
ሀገርን ለመምራት ነን ብንለው ብቁ
አንገቱን ጠምዝዞ አይቀርም መሳቁ

ብርቱካን ትፈታ ማንም አይታሰር
እኛም እንላበስ ሠላምና ፍቅር።



እላይ የነደደው ፀብ ጥላቻ ከፍቶ
ህዝቡን አለያይቷል ከሀገር ሀገር ዘምቶ
በዚሁ ምክንያት ፍቅርን አርቀነው
ትግሉን የኋልዮሽ ጎትተን አቆምነው።
አንደኛ እየሆንን ለየብቻ መሮጥ
እንዴት ያቅተናል ተባብረን መዘርጠጥ

ሰነፎች አንባል ኣላነሰን አቅም?
ወይን አልቀጠነ ከነሱ የኛ ደም?
እንደምን ተሳነን በዳይ ላይ ለማደም?
ተባብረን ለመሥራት በሉ ቃል እንግባ
ይኼን አጽድቁልኝ እስቲ በጭብጨባ።




አዎን ይፈቱልን የኅሊና እስረኞች
በሆነ ባልሆነ አይጠቁ ዜጎች
ብርቱካን ትፈታ ማንም አይታሰር
በአንድነት እንቁም እኛም ይዘን ፍቅር።

ተብሏል ከፊትም ቀና ነው መንገዱ
ተባብረው ተማክረው አንድ ላይ ሲሄዱ
"ብርቱካን ትፈታ!" – "ትውጣ ከጭለማ!"
ማለት ብቻ ሳይሆን የትግሏን ዓላማ
አንግበን እንውጣ አለን በቂ አቅም
እናሸንፋለን እልፍ ነን አንወድቅም።
ላገራችን ስንል ጥላቻን እንግደፍ
ሽኩቻችን ይቁም ይብቃን መጠላለፍ።




ህዝቡ የመረጠው የሰቀለው መሪ
ትግሉን የሚጎዳ ከሆነ አስቸጋሪ
ከቦታው አንስቶ እሱኑ መንቅሎ
የትግሉን ጎዳና መሄጃ አስተካክሎ
አለምንም ችግር መቀጠል ይቻላል
የግለሰብ ጭራ ሆኖ ከመከተል።
ይፈቱ በቶሎ የኅሊና እስረኞች
በሆነ ባልሆነ አይጠቁ ዜጎች
ብርቱካን ትፈታ ማንም አይታሰር
በአንድነት እንቁም እኛም ይዘን ፍቅር።



እኛኑ እኛው ከሰን - እኛኑ እኛው ወቅሰን
አትድረስ አልደርስም ብለን ተለያይተን
ችግሩን ስቃዩን የህዝቡን መረገጥ
ከአምናው ዘንድሮ አባስንበት ይበልጥ
በዚሁ መጠን ግን መልካም ጥሩ ዜጋ
በሐቅ የሚታገል መኖሩን አንዘንጋ
እዚሁ ተጣልተን እዚሁ ተማምነን
እዚሁ ተታርቀን ትግሉን አጎልበተን
በግልጽነት መጓዝ መሄድ እንችላለን
አለበለዚያ ግን ተቃርነን ከስሙ
ምኑ ነው አንድነት የቱ ነው ሠላሙ?!
ብለው ቢጠይቁን እንዳያንሰን አቅሙ።
በይፋ እንወያይ ይብቃን መወሻሸቅ
ፍቅርን እንዝራ ጥላቻን እናርቅ።



የብርቱካን ትግል የአንድነት ዓላማ
መንገዱን እንዳይስት እንዳይሆን ጠማማ
በሆነ ባልሆነው አንናጭ እርስ በእርስ
በውይይት ፈተን በእርቅ እንታደስ።
ወዳጅ የሆነንን ጥፋቱን ሸፍነን
ወዲያው እንደመንገር በይሉኝታ ታጥረን
በዳዩ ጥፋቱን አውቆት ሳይረዳ
በተጣላን ጊዜ አውጥተን ከጓዳ
ከሌላ ክስ ጋር አብረን ከመለጠፍ
ገና ከመነሻው እያየን አንለፍ
ቅር ያለንን ይዘን ሆዳችንን ከማመቅ
በተገቢው ስፍራ ፊት ለፊት እንጠይቅ።
ሦስት ወራት ተስማምተን እንቆይና በሰልፍ
በድንገት ተጣልተን ዓመት ስንኳረፍ
ትግሉ እራሱ ደክሞት አሸለበው እንቅልፍ
እንዲህማ ባይሆን ይሄ ባይፈጠር
ቅስቀሳ ኮሚቴ አያሻንም ነበር።
በሙሉ ተስማምተን ብንልማ "በቃ!"
ምን ይሠራ ነበር? የትግል አለቃ



መለያየት አዝሎ ፀብ ከበላይ ሲወርድ
ባላወቅነው ዘፈን እኛ እስክስታ አንውረድ።
የሚገርመው ነገር አድርጎብን ዕድል
ፀብ ይላክልናል መመሪያ ይመስል


ወለላዬ ከስዊድን welelaye2@yahoo.com

አሁንም ካልቆመ ከቀጠለ ፀቡ
ምን እንደምናደርግ እንምከር ባግባቡ
ሁሉንም በቅድሚያ ቀድመን ካሰብንበት
በቂ ጊዜ ወስደን ከተማከርንበት
አዲስ ነገር አድርገን አንገጥምም ጦርነት።




ታግለን ቶሎ እናምጣ ዲሞክራሲ ሠላም
እኔም ነፃ ልውጣ ስለውበት ልግጠም
እያለቀብኝ ነው ማውገዣ አማርኛ
ካልጻፍኩኝ በስተቀር ደግሞ በትግሪኛ
ፈካ ብሎ ፊቴ ደስ ብሎኝ ሳልስቅ
ሃያ ዓመት ሊሞላኝ ቀረኝ አንድ መንፈቅ
ይሄንን እያየ ልጄ እንኳን ተሳቅቆ
አንድ ቀን አየሁት ሲስቅ ተደብቆ
ይሄ በእኔ ብቻ አይደለም የመጣ
በትግሉ እንግፋበት እኛም ነፃ እንውጣ።



“ብርቱካን ትፈታ!” ብለን ስንነሳ
የምንጠይቀውን ሌላውን አንርሳ።
ሕግ የተከተለ ነፃ ምርጫ እንዲኖር
የህዝቡ ፍላጎት ድምፁም እንዲከበር
ቦታው እንዲመለስ የፊት ድንበራችን
መቸብቸቡ እንዲያቆም ለሙ መሬታችን
የዲሞክራሲ መብት የፕሬስ ነፃነት
መከበር እንዲችል የህዝብ እኩልነት
ይጠበቅብናል እጅግ ብዙ መሥራት።
ብርቱካን ትፈታ ማንም አይታሰር
በአንድነት እንቁም እኛም ይዘን ፍቅር።

